# አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ

# የ2018 የግብር ዘመን የማሳወቂያ ጊዜ

## የሂሳብ መዝገብ የማይዙ ግብር ከፋዮች የሚስተናገዱበት የአሰራር ስርዓት

መስከረም 2019 ዓ/ም

## I. የሂሳብ መዝገብና የሂሳብ መግለጫ መሰረት በማድረግ የማሳወቅ የመክፈል እና ሰነዶችን የመያዝ ግዴታ ተፈጻሚ የማይደረግባቸው ግብር ከፋዬች

የተሻሻለው ፌደራል ገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 1395/2017 አንቀጽ 3/ሀ እና አንቀጽ 6 እና የፌደራል ገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 አንቀጽ 21፣ 33 እና 82 እንዲሁም በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 17 መሰረት የሂሳብ መዝገብና የሂሳብ መግለጫ መሰረት በማድረግ የማሳወቅ፣ የመክፈል እና ሰነዶችን የመያዝ ግዴታ አመታዊ አጠቃላይ ገቢን መሰረት አድርጎ በደረጃ "ሀ" እና የተሻሻለው ፌደራል ገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 1395/2017 አንቀጽ 3/ሀ እና አንቀጽ 6 በደረጃ "ለ" ግብር ከፋዬች ላይ የተጣለ ሲሆን በርካታ ግብር ከፋዬችም ይህንኑ መሰረት አድርገው ግዴታቸውን በመወጣት ላይ ይገኛሉ፡፡ ይሁን እንጂ የተወሰኑ ግብር ከፋዬች በህጉ የተጣለባቸውን ግዴታ ለመወጣት የተሰማሩበትን የስራ ዘርፍ ባለው የተለየ ባህሪ ምክንያት መቸገራቸውን በተለያየ ጊዜ በመጥቀስ አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም የግብር ሕጉ ለየትኛውም የንግድ ዘርፍ በተለየ መልኩ የሂሳብ መዝገብና የሂሳብ መግለጫ መሰረት በማድረግ የማሳወቅ የመክፈል እና ሰነዶችን የመያዝ ግዴታን ቀሪ አላደረገም፡፡ በመሆኑም ይህንኑ በታክስ አስተዳደር አዋጅ 983/2008 አንቀጽ 102 ግዴታ አለመወጣት አስተዳደራዊ ቅጣት የሚያስከትል መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የተለየ ባህሪ ያላቸው የተወሰኑ የሥራ ዘርፎች የግብር ህጉን ድንጋጌዎች በአስከበረ አግባብ የገቢ አሰበሰቡን እና የአገልግሎት አሰጣቱን ፍታሀዊነት ማዕከል ያደረገ የአሰራር ሥርዓት ለ2018 የግብር ማሳወቂያ ጊዜ ሂሳብ መዝገብ የማቅረብ ግዴታን ተፈጻሚነት ለመጨረሻ ጊዜ እንዲሆን እና ለቀጣይ በጀት ዓመት የሂሳብ መዝገብ እንዲይዙ ቃለ-መኃላ እንዲፈርሙ በማድረግ እና አስተዳደራዊ ቅጣትን በተመለከተ ሰነድ ባለመያዝ የሚጣለዉ ቅጣት ተፈጻሚ ይደረጋል፡፡

1. ግብር ከፋዮች ግንዛቤ የተለየ ድጋፍ የሚፈልጉ እና ሥራዎች ከመንግስት ጋር በተገበ ውል ብቻ የሚያከናወኑ በማህበር የተደራጁ የትምህርት ቤቶችና የምገባ ማዕከላት መጋቢ እናቶች፣ በልዩ ሁኔታ ከመንግስት ጋር ውል ያላቸው ግብር ከፋዮች፣ በከተማ ጽዳትና ውበት፣ ደረቅ ቆሻሻ እና ገፀ-ምድር ማስዋብ ላይ የተሰማሩ፣ ከንግድ ቢሮ ትስስር የተፈጠረላቸው የሸገር ዳቦን የሚሸጡ ማህበራት፣ ከመንግስት ተቋማት ጋር ያላቸውን ውልና በበጀት ዓመቱ ከአሰራቸው የመንግስት ተቋም ዓመቱ ውስጥ

የተከፈላቸውን ክፍያ የሚገልጽ መረጃ ሲያመጡ በደንብ 410/2009 መሰረት አድረጎ ለስንጠረዥ "ሐ" መሰረት ግብሩ ይሰላል።

2. የሸገር ዳቦ የሚሸጡ በተጓዳኝ የሚከናወኑ የንግድ ስራዎች መኖራቸውን በመስክ ምልከታ ተረጋግጦ ተጨማሪ እየሰሩት ያለው ስራ እንዲወሰን ይደረጋል።
3. ጫኝ እና አውራጅ፣ ኢትዮጵያ መብራት ኃይል የኤሌክትሪክ የፖል ጉድጓድ ቁፋሮ፣ በማህበር ተደራጅተው በጥበቃ ስራ ላይ የተሰማሩ፣ የታክሲ ታራ አስከባሪ የሂሳብ መዝገብ መያዝ ሲጠበቅባቸው ያልያዙ ግብር ከፋዮች ለዘርፉ የተቀመጠውን የትርፍ ህዳግ ተወስዶ እንዲወሰን ይደረጋል።
4. በተሻሻለው የገቢ ግብር አዋጅ 1395/2017 መሠረት ንግድ ሥራ ፍቃድ ሳይኖራቸው በሞያ ፍቃድ ብቻ አገልግሎት የሚሰጡ ጠበቆች፣ የኢንሹራንስ ወኪሎች፣ ኢንሹራንስ ጉዳት ገማቶች እንዲሁም በአጠቃላይ በአዋጁ የተዘረዘሩት 8ቱ ዘርፎች የሂሳብ መዝገብ መያዝ የሚገደዱ ሲሆን ሂሳብ መዝገብ ካላቀረቡ የሚያወጡት ወጪ ተቀናሽ የሚደረግበት ሁኔታ ሚኒስትሩ መመሪያ እንደሚያወጣ የተደነገገ ቢሆንም እስካሁን መመሪያ በለመውጣቱ ቀደም ሲል በተጠኑ ጥናቶች መሠረት ከጠቅላላ ገቢያቸው ላይ 35% እንደ ወጪ 65% ግብር የሚከፈልበት ገቢ ሆኖ በሠንጠረዥ "ሐ" መሠረት ግብሩን በማስላት ገቢውን መሰብሰብ ቢቻል፤
5. የደረጃ "ሀ" ግብር ከፋዮች በትራንስፖርት ዘርፍ የተሰማሩ ግብር ከፋዮች በ2017 የግብር ዘመን ወይም በ2016 የግብር ዘመን 57% የዋጋ ግሽበት ማስተካከያ ግብር የተከፈለበትን በማድረግ አጠቃላይ ገቢ ለ2018 ግብር ዘመን ግብር ለመወሰን ለደረጃ "ለ" ግብር ከፋዮች የተቀመጠውን የአሰራር ስርዓት እና ቀመር ተግባራዊ ይሆናል።
6. በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/08 መሠረት ደረጃ "ለ" እና ደረጃ "ሐ" የነበሩ እና በአዲሱ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 1395/17 መሠረት ወደ ደረጃ "ሀ" ያደጉ ግብር ከፋዮችን በተመለከተ በ2017 ግብር ዘመን ለንግድ ሥራ ገቢ ግብር እና የተርን ኦቨር የተከፈለ ወይም ሊከፈል የሚገባው ታክስ በመውሰድ በደረጃ "ለ" አሰራር ስርዓት መሠረት በማስላት ግብሩ የሚከፍሉ ይሆናል።
7. በግምት ግብር አወሳሰን አዋጅ ቁጥር 138/2010 የደረጃ "ሀ" የንግድ ቤት እና የመኖሪያ ኪራይ ገቢ ግብር ከፋዮችን በተመለከተ ሂሳብ መዝገብ መያዝ [illegible]

ያላቀረቡ ግብር ከፋዮች 35% እንደ ወጪ ወይም 65% እንደ ገቢ ተወስዶ ታክሱ የሚሰላ ይሆናል።

8. በአዲሱ ገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 1395/2017 አንቀጽ 23 አማራጭ አነስተኛ ለደረጃ "ሀ" ግብር ከፋዮች 2 ሚሊዮን አማራጭ አነስተኛ ግብር 2.5% ጋር ተነፃፅሮ የተሻለው ተወስዶ የሚወሰን ይሆናል።

## II. ለ. የሂሳብ መዝገብና የሂሳብ መግለጫ መሰረት በማድረግ የማሳወቅ የመክፈል እና ሰነዶችን የመያዝ ግዴታን ያልተወጡ

የተሻሻለው ፌደራል ገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 1395/2017 አንቀጽ 3/ሀ እና አንቀጽ 6፣ አንቀጽ 50/ለ የደረጃ "ሀ" ግብር ከፋዮች የፌደራል ገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 አንቀጽ 21፣ 33 እና 82 እንዲሁም በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 17 መሰረት የሂሳብ መዝገብና የሂሳብ መግለጫ መሰረት በማድረግ የማሳወቅ" የመክፈል እና ሰነዶችን የመያዝ ግዴታ አመታዊ አጠቃላይ ገቢን መሰረት አድርጎ በደረጃ "ሀ" እና በደረጃ "ለ" ግብር ከፋዬች ላይ የተጣለ ሲሆን በርካታ ግብር ከፋዬችም ይህንኑ መሰረት አድርገው ግዴታቸውን በመወጣት ላይ ይገኛሉ፡፡ ይሁን እንጂ የሂሳብ መዝገብ መግለጫ መሰረት በማድረግ የማያሳወቅ" የመክፈል እና ሰነዶችን የመያዝ ግዴታ የማይወጡ ከላይ በዝርዝር ከተገለጹ ዘርፎች ውጭ ያሉ ግብር ከፋዬች ግብር ለመሸሽ የሚደረግ ድርጊት መሆኑ ከግምት ውስጥ ገብቶ መዝገብ አለመያዝ ምርጫ በማሆንበት ደረጃ አስተማሪ የሆነ እርምጃ በግብር ህጉ መሰረት መወሰድ ገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 አንቀጽ 80 መሰረት በደንብ ቁጥር 410/2009 ለደረጃ ‹‹ሐ›› የተቀመጠውን የማትረፊያ ህዳግ በእጥፍ እና ቅጣትም በአንቀጽ 109 እና 110 መሰረት የታክስ ጉለቱን 40 በመቶ እና የታክሱን 200% በመቅጣት ህጉን ተፈጻሚ ማድረግ ተገቢ ይሆናል፡፡ በመቀጫ የተስተናገዱ ግብር ከፋዮች መረጃው ተደራጅቶ ለህግ ተገዥነት ዘርፍ መተለላፍ አለበት፡፡

ይህ አሰራር ስርዓት ተግባራዊ የሚሆነው ለ2018 የግብር ዘመን ብቻ መሆኑ ታውቆ የሂሳብ መዝገብ ማቅረብ ሲገባቸው ያላቀረቡ ግብር ከፋዮች ወደፊት የሂሳብ መዝገብ ለመያዝ ቃለ -መኃላ እንዲፈርሙ በማድረግ የሚስተናገዱ ይሆናል።